# ኢትዮጵያን ሥጋት ላይ የጣላት የሥነ ምህዳር ቀውስ

ከክርስቶስ ልደት በፊት 2000 ዓመት ገደማ ጥንት ሜሶፖታሚያ ተብላ በምታወቀው አገር ለም የነበረው የሃቡር ምድር ወደ በረሃነት ተለወጠ። በስፋቱ በአፍሪቃ አህጉር አንደኛ በዓለም ደግሞ ሁለተኛ የሆነው የሠሃራ በረሃ ድሮ ለግጦሽ መሬት ያገለግል እንደነበረ ዋቢ መረጃዎች ይጠቁማሉ። አሁን የሚታዬው ሁኔታ በአስቸኳይ ካልተገታ በስተቀር አገራችን ኢትዮጵያም ከፍተኛ የሥነ ምህዳር ቀውስ ሰለባ መሆኗን ለመተንበይ አዳጋች አይደለም። የመጀመሪያው የሰው ልጅ ዝርያ በሁለት እግሩ ቆሞ የሄደባት ጥንታዊት አገር የደን፣ የአፈርና የብዝሃ ህይዎት ሃብቷ በብርሃን ፍጥነት እየተሟጠጠ መሄዱን በእኛ ዕድሜ እየተመለከትነው ያለ ገሃድ ነው።

የደን መጨፍጨፍ የሃገራችንን ህልውና ሊፈታተኑ የቻሉ የሥነ ምህዳር አደጋዎች እንዲከሰቱ ዐቢይ ሚና ተጫውቷል። ደኖች ሲመነጠሩ ተራሮች፤ ኮረብቶችንና አምባዎች ተራቆቱ። በተክሎቻቸው አማካይነት የፀሃይን ሃይል በመጠቀም ምግብ የመሥራት ክህሎታቸው ተረት ሆነ። በምግብ ሰንሰለት ቁርኝቱ ውስጥ ሊጫወቱ ይገባ የነበረውን ምርታማነት እስከወዳኛው አጡትና የጨረቃ መሬት መሰሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት በውሃ ሃይል ተሸርሽሮ ከአካባቢው የሚጠፋው የአፈር መጠን ተፈጥሮ ከሚተካው በእጅጉ ያነሰ በመሆኑ ነው። በየዓመቱ ለጎርፍ ሰለባ የሚሆነው ለም አፈር 2 ቢሊዮን ቶን እንደሚደርስ ሲገመት አገራችን ከሃይቲ ቀጥሎ ከፍተኛ ሥነ ምህዳራዊ ቀውስ የገጠማት አገር ተብላ እንድትፈረጅ አድርጓታል።

የተለያዩ በኢትዮጵያ የአካባቢ ገጽታ ላይ ተመርኩዘው የተካሄዱ ጥናቶችን በመፈተሽና ከራሴ ልምድ በመነሳት አሁን ኢትዮጵያ የገጠማት ሥነ ምህዳራዊ ቀውስ የተከሰተው በማወቅና ባለማወቅ መካከል ባለው ልዩነት ሳይሆን አደጋውን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ዕርምጃ በመውሰድና ባለመውሰድ መካከል በተፈጠረው ሰፊ ልዩነት ነው የሚል ግምት አለኝ።

ይህ በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበበውን የሥነ ምህዳር ቀውስ መከላከል ብሎም ማስወገድ ይቻላል ወይ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚቻለው ችግሩን ለመፍታት በምንወስደው ርምጃ ላይ ተንተርሶ ነው። በተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወሰዱ ርምጃዎች አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡበት ሁኔታ እንዳለ ይስተዋላል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ለዘመናት ተንከባክባ የያዘቻቸው ደኖች በጉግል ማፕ አማካይነት በተራቆተው የአገሪቱ ክፍል መካከል አረንጓዴ ግርማ ሞገስ ተላብሰው በግልጽ ይታያሉ።



የኮንሶ ገበሬዎች የተለያዩ አገር በቀል የሥነ ምህዳር ዘዴዎችን በመጠቀም የርሻ መሬታቸው ከ3 ሽህ ዓመታት በላይ ለምነቱን ጠብቆ እንድቆይ አድርገዋል። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ቅዝቃዜ በሚከሰትባቸው ወራት ሌሊት ሰማዩ ሲጠራ አዝመራ በውርጭ እንደሚጠቃ የተማረው ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ካልተማሩ ወላጆቹ አንደበት ነው።

ድህነት የተጫነው ህብረተሰብ በአካባቢው የቆምችውን የመጨረሻውን ዛፍ ለመቁረጥ ስለሚገደድ የደን ልማትና ጥበቃ እልህ አስጨራሽ ሥራ መሆኑ አያጠያይቅም። ይሁን እንጅ በቤ/ክርስቲያን አካባቢ የሚካሄድ አነስተኛ የተክሎች ክብካቤ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ይታመናል። ለምሣሌ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ዕምነት ተከታዮች መንግሥት ከሚያወጣው ህግ ሲነጻጸር ለሃይማኖታዊና ባህላዊ ህጎች የተሻለ ተገዥነት እንደሚያሳዩ ተዘግቧል።

በኦርቶዶክስ ቤ/ተ ክርስቲያናት የሚገኙትን ብርቅ ደኖች ተንከባክበው ያቆዩልን አባቶቻችን ለልጆቻቸው ስጦታ፣ ለዓለም ህብረተሰብ ደግሞ ገፀበረከት የለገሱ መሆኑን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። በዚህ ረገድ Tree Foundation እነዚህን ደኖች ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ የጀመረው ፕሮጀክት በአርአያነት የሚጠቀስ ነው። የሚከተለው መርሃ ግብር “በአንድ ወቅት አንድ ቤ/ተክርስቲያን” የሚል ሆኖ በመላ ሃገሪቱ ተሰራጭተው የሚገኙትን ቁጥራቸው ወደ 35 ሽህ የሚጠጋ የኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ደኖች ላይ የዕፅዋትና እንስሳት የረጅም ጊዜ ሳይንሳዊ ምርምር ለማካሄድ እ.ኤ.አ. በ 2009 ዓም ጉዞውን አንድ ብሎ መጀመሩን የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር ሎውማን ገልጸዋል።

ወርቁ ለገሠ ሙላት(PhD)

ተባባሪ ፕሮፌሰር